# የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ

# ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL

ኢሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው::

**EHRCO stands for democracy, the rule of law and the respect of human rights.**

ጥቅምት 20 ቀን 2000 ዓ.ም

## 103ኛ ልዩ መግለጫ

## የሕግ የበላይነት ይከበር!

### መግቢያ

ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች አለም ዐቀፍ ቃልኪዳን አንቀጽ 9(1) እያንዳንዱ ሰው የግል ነጻነትና ደህንነት መብት እንዳለው በማረጋገጥ ማንም ሰው ከህግ ውጭ አይያዝም፣ አይታሰርም ይላል:: በወንጀል የተጠረጠረ ሰውም ቢሆን ፍ/ቤት ቀርቦ ዳኝነት የማግኘት ያለዚያ ደግሞ የመለቀቅ መብት እንዳለው የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 3 ይደነግጋል::

የኢፌዲሪ ህገ-መንግስትም በአንቀጽ 17 (2) ላይ «ማንኛውም ሰው በህግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም» ሲል በማያሻማ ሁኔታ ይደነግጋል::

ይሁን እንጂ እነዚህን ህገ-መንግስታዊና ዓለምአቀፋዊ ድንጋጌዎች በሚቃረን መልኩ በርካታ ግለሰቦች በህግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ተይዘው፣ ክስ ሳይቀርብባቸው ወይም ሳይፈረድባቸው በተለያዩ እስር ቤቶች ውስጥ በተለይም በማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ መምሪያ ውስጥ ታስረው እንደሚገኙ የታሳሪ ቤተሰቦች ለኢሰመጉ አመልክተዋል::

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ(ኢሰመጉ) በዚህ 103ኛ ልዩ መግለጫው ከተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎችና በአዲስ አበባ ከተማ ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ጋር ግንኙነት አላችሁ፤ ደጋፊዎች ናችሁ በሚልና በተለያዩ ምክንያቶች ዜጎች ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ እንደሚታሰሩ፣ ፍርድ ቤት ከቀረቡም በኋላ ቢሆን ፖሊስ ተደጋጋሚ የጊዜ ቀጠሮ ጠይቆ በተጠርጣሪዎች ላይ በቂ ማስረጃ ማቅረብ ባለመቻሉ ፍርድ ቤት መዝገቡን ዘግቶ ያሰናበታቸው፣ እንደዚሁም ፍርድ ቤት በዋስ እንዲለቀቁ ትእዛዝ ቢሰጥም ፖሊስ ግን የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ ባለማክበሩ ይህ መግለጫ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ከእስር ሳይፈቱ ስለሚገኙ ዜጎች ያሰባሰበውን መረጃ እንደሚከተለው አቅርቧል::

### ዝርዝር

ቢልሱማ ሹጊ በቦሌ ክፍለ ከተማ ከቤተሰቦቹ ጋር የሚኖር በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ውስጥ ሯጭ እና የ18 አመት ወጣት ሲሆን ሐምሌ 27 ቀን 1999 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 3 ሰአት ሲሆን የካ አካባቢ ከጓደኞቹ ጋር ሩጫ ልምምድ ላይ እያለ የፌዴራል ፖሊስ አባሎች "የኦነግ ደጋፊ ነህ" በማለት ያለፍ/ቤት ትእዛዝ ይዘውት ቦታውን ለይቶ በማያውቀው ያቤሎ ዞን ሞያሌ አካባቢ እንዲሄድ ተደርጎ ለአንድ

ሳምንት በረሃ ውስጥ እንዳቆዩት፣ እንዲሁም ጆሮውና እግሩ ላይ ድብደባ እንደተፈፀመበትና ጉዳት እንደደረሰበት ቤተሰቦቹ ገልፀዋል:: ይህ ሁሉ ሲሆን ቤተሰቦቹ የት እንዳለ የማያውቁ የነበረ ሲሆን ለአንድ ወር ያህል ሲያፈላልጉት ቆይተው አዲስ አበባ ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ መምሪያ በእስር ላይ እንዳለ ማወቃቸውን ገልጸው፣ ታሳሪው ለስምንት ጊዜ ያህል በጊዜ ቀጠሮ አራዳ ምድብ ችሎት እንደቀረበና ለመጨረሻ ጊዜ ጥቅምት 3 ቀን 2000 ዓ.ም ፍ/ቤት እንዲቀርብ ተደርጎ ፍ/ቤቱም በቂ ማስረጃ አልቀረበም በማለት ፋይሉን የዘጋው ቢሆንም ይህ መግለጫ እስከተጠናቀረበት ድረስ ሳይለቀቅ በእስር ላይ እንደሚገኝ የታሳሪው ቤተሰቦች ለኢሰመጉ አመልክተዋል::

በተመሳሳይም ስማቸው ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ የተዘረዘረዉ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዴን) አባላት እና ደጋፊዎች የሆኑ ግለሰቦች ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ጋር ግንኙነት አላችሁ ወይም ትደግፋላችሁ በሚልና በተለያዩ ምክንያቶች ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዲታሰሩ ከተደረገ በኋላ በተደጋጋሚ የጊዜ ቀጠሮ ፍ/ቤት ቀርበው ፍ/ቤቱ በቂ ማስረጃ አልቀረበም በማለት ፋይሉን የዘጋው ቢሆንም ይህ መግለጫ እስከተጠናቀረበት ድረስ ፖሊስ እንዳልለቀቃቸውና በአዲስ አበባ ማእከላዊ ወንጀል ምርመራ ታስረው እንደሚገኙ ኦፌዴን በ04/02/2000 ዓ.ም በቁጥር O.F.D.M/100/617 በተጻፈ ደብዳቤ ለኢሰመጉ አመልክቷል::

ሰንጠረዥ1

| ተ.ቁ | ስም | በቁጥጥር ስር የዋሉበት ቦታ | ፍ/ቤት መዝገቡን የዘጋበት ቀን |
|---|---|---|---|
| 1 | ጂአድ ሰኢድ | መቱ | 29/12/1999 |
| 2 | ወንድሙ ፍቅሬ | በደሌ | 02/13/1999 |
| 3 | ካሳሁን አሰፋ | መቱ | 29/12/1999 |
| 4 | ተሾመ አባተ | መቱ | 29/12/1999 |
| 5 | ሚካኤል እምሩ | አዲስ አበባ | 23/01/2000 |
| 6 | ወልዴ ቶሎሳ | አዲስ አበባ | 07/02/2000 |
| 7 | ሙዘይን ሚዛና | አዲስ አበባ | 07/02/2000 |
| 8 | ታምራት ደምሴ | በደሌ | 07/02/2000 |
| 9 | ከሊፋ አባፎጊ | ጅማ | 07/02/2000 |
| 10 | ኢትዮጵያ ተመስገን | ጅማ | 07/02/2000 |
| 11 | ቶላ መርዳሳ | በደሌ | 07/02/2000 |
| 12 | ሽብሩ ታሲሳ | ጨዋቃ | 07/02/2000 |
| 13 | ሳልስም አይናለም | በደሌ | 30/01/2000 |
| 14 | መሰረት ቢኖር | በደሌ | 30/01/2000 |
| 15 | ሙዘይን ጉደታ | በደሌ | 02/13/1999 |
| 16 | ጂራታ ደበላ | መቱ | 02/13/1999 |
| 17 | ሞገስ ከበደ | አዲስ አበባ | 02/13/1999 |

ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘረው ግለሰቦች ደግሞ ከላይ በሰንጠረዥ1 ከተመለከቱት ግለሰቦች ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ታስረው በሀምሌ ወር 1999 ዓ.ም በፍ/ቤት የዋስትና መብታቸው የተከበረላቸው ቢሆንም ይህ መግለጫ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ፖሊስ እንዳልለቀቃቸውና በአዲስአበባ ማእከላዊ ወንጀል ምርመራ ታስረው እንደሚገኙ ኦፌዴን ከላይ በተጠቀሰው ደብዳቤ ጨምሮ አመልክቷል፡፡

ሰንጠረዥ2

| ተ.ቁ | ስም | በቁጥጥር ስር የዋሉበት ቦታ | ፍ/ቤት መዝገቡን የዘጋበት ቀን |
|---|---|---|---|
| 1 | ሸሪፍ ኢብራሂም | ጂማ | ሀምሌ ወር 1999 ዓ.ም |
| 2 | ፍቃዱ ቡልቲ | ’’ | ’’ |
| 3 | አዱኛ ባልቻ | ’’ | ’’ |
| 4 | ግርማ ተስፋዬ | ’’ | ’’ |
| 5 | ዳዊት ቀነአ | ’’ | ’’ |
| 6 | መሀመዲ አባነጋ | ’’ | ’’ |
| 7 | መሀመድ ሲራጅ | ’’ | ’’ |
| 8 | ቶላ ጫሊና | አዲስ አበባ | ’’ |

## ማጠቃለያ

- ከዚህ በላይ በዝርዝር እንደተመለከተው ታሳሪዎቹ በተጠረጠሩበት ወንጀል በፍ/ቤት ተደጋጋሚ የጊዜ ቀጠሮ ከተጠየቀባቸው በኋላ ማስረጃ ስላልቀረበባቸው ፍ/ቤት መዝገቡን ቢዘጋውም ፖሊስ ግን ሊለቃቸው አልቻለም፡፡ የዋስትና መብታቸው በፍ/ቤት የተከበረላቸውም ለወራት ከህግ አግባብ ውጪ በእስር እየተንገላቱ ይገኛሉ፡፡

- ይህ ደግሞ በአገሪቱ ህገመንግስት የተቀመጠውን የህግ የበላይነት በግልጽ የሚጻረር ተግባር በመሆኑ ኢሰመጉን በእጅጉ ያሳስበዋል፡፡

- ከዚህም በተጨማሪ ታሳሪዎች የሚገኙት በበቂ ሁኔታ ከቤተሰቦቻቸውም ሆነ ከሌላ ጠያቂ ጋር በማይገናኙበት በአዲስ አበባ ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ በመሆኑ ኢሰመጉ ለደህንነታቸው ይሰጋል፡፡

- ስለሆነም መንግስት በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉ መብቶችን የማስከበር ኃላፊነት ስላለበት ፍ/ቤት ነጻ ያደረጋቸውን፣ እንዲሁም ፍ/ቤት የዋስትና መብታቸውን ያከበረላቸውን ዜጎች በአፋጣኝ ከእስር እንዲለቀቁ እንዲያደርግ እንጠይቃለን፡፡

በተጨማሪም ለሰብአዊ መብቶች መከበርና ለሕግ ልዕልና የቆማችሁ ዜጎች፣ ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የመንግሥታትና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች የኢትዮጵያ መንግስት በአገሪቱ ህገመንግስት የተረጋገጡትን መብቶች እንዲያከብርና በህግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ተይዘው፣ ክስ ሳይቀርብባቸው ወይም ሳይፈረድባቸው በማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ መምሪያ ታስረው የሚገኙ ዜጎች በአፋጣኝ ከእስር እንዲለቀቁ የበኩላችሁን ግፊት እንድታደርጉ ኢሰመጉ ይጠይቃል።

ግልባጭ

- **ክቡር አምባሳደር ተሾመ ቶጋ**
  *የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈ-ጉባኤ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 80001፣ ፋክስ (251-1) 124 1004*
  *ስልክ ቁጥር (251-1) 124 1018*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ ደግፌ ቡላ**
  *የኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈ-ጉባኤ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 80001፣ ፋክስ (251-1) 1242304*
  *ስልክ ቁጥር (251-1) 124 2301*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ**
  *የኢፌዲሪ ኘሬዚዳንት*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1438፣ ፋክስ (251-11) 155 2020*
  *ስልክ ቁጥር (251-1) 551 8850*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ**
  *የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1031፣ ፋክስ (251-11) 155 2020*
  *ስልክ ቁጥር (251-1) 122 6767*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ ሲራጅ ፈርጌሣ**
  *የኢፌዲሪ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1370፣ ፋክስ (251-11) 552 0000*
  *ስልክ ቁጥር (251-1) 552 0000*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ አሰፋ ከሲቶ**
  *የኢፌዲሪ የፍትሕ ሚኒስትር*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1370፣ ፋክስ (251-11) 554 5716*
  *ስልክ ቁጥር (251-1) 551 5099*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ ወርቅነህ ገበየሁ**

***የፌዴራል ፖሊስ ዋና ዳይሬክተር***
***ፖ.ሣ.ቁጥር 199፣ ፋክስ (251-1) 153 4253***
**ስልክ ቁጥር (251-1) 551 2744**
**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

- **ክቡር ኮሚሽነር በፈቃዱ ሰቦቃ**
  **የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር**
  ***ፖ.ሣ.ቁጥር 5647 ፣ ፋክስ (251-1) 155 0360***
  **ስልክ (251-1) 156 0115**

- **ክቡር አምባሳደር ካሣ ገ/ሕይወት**
  **የኢፌዲሪ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር**
  ***ፖ.ሣ.ቁጥር 1165፣ ፋክስ (251-1) 618 0041***
  **ስልክ ቁጥር (251-1) 618 0040**
  **አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

- **ክቡር አቶ አባይ ተክሌ**
  **የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ዋና እምባ ጠባቂ**
  ***ፖ.ሣ.ቁጥር 2459፣ ፋክስ (251-1) 553 2073***
  **ስልክ ቁጥር (251-1) 553 2053**
  **አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**